# የትንቢት ቃል

ሶስተኛ ዓመት, ቁጥር 2

ሰኔ 2001


## የምጽአቱ ተስፋ

**«የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመለሳል» አሏቸው።** (ሐዋ 1፣11)

የመለያየት ቀን ደረሰ። የሱስ ከመቃብር ከተነሳ ከአርባ ቀናት በኋላ ወደ አባቱ ሊመለስ ነው። ስለ አብና ስለ ሰማይ መንግሥት ለደቀመዛሙርቱ ነግሮአቸዋል። የሰማይ መንግሥት የብርሀን፣ የሰላምና የፍቅር መነግሥት እንደሆነ መስክሮላቸዋል። እርሱ ወደ ሰማይ ሲመለስ ተከታዮቹ ግን በዚህች በጨለማ፣ በኃጢአት፣ በግፍና በተንኮል በተበከለች ምድር ላይ ይቀራሉ። ከመንፈስና ከአካል ደዌ የፈወሳቸው ሰዎች፣ በብቸኝነታቸው የረዳቸውና ያጽናናቸው ነፍሳት ስለ ትንሳኤው የሰሙትን የምሥራች ገና ሳይጠግቡ ይኸው አዳኙ ሊለያቸው ነው። እኒያ ህፃናትን የባረኩና ተአምራትን ያደረጉ በመጨረሻም በመስቀል ላይ የተቸነከሩት እጆች ለመጨረሻ ጊዜ ነፍሳትን ለመባረክ ተዘጋጁ። «ረቡኒ» የሚሉት ክርስቶስ አስተማሪአቸው ብቻ ሳይሆን አዳኝም እንደሆነ በመስቀል ላይ ፍቅሩን ያስመሰከረው ፣ ይህ የዘመናት ሁሉ ምኞት የሆነው ጌታ ደብረ ዘይት በምትባለው ተራራ ላይ ደመና ልትቀበለውና ወደ ሰማይ ሊያርግ ነው።

በርግጥ ኃጢአት ወደ ዓለም ባይገባ ኑሮ «ስንብት» የሚባል ነገር ባልኖረ ነበር። ስለዚህ ኃጢአት ለዘለአለም እስካልጠፋ ድረስም ስንብት አይጠፋም። የስንብት ዋና አስከፊ መልኩ ደግሞ ሞት ነው። ሁሉም በየተራው ወደ ቀዝቃዛው መቃብሩ ይሄዳል። ይህም እስከ ሙታን ትንሳኤ ድረስ የመጨረሻው ስንብት ነው። ጌታ የሱስ ይህንን «ሞት» የሚባለውን ጠላት ድል ነስቶ ከመቃብር ስለተነሳ እና ሕያው ስለሆነ ሞት የተሸነፈ ጠላት ሆነ።

እነዚህ የገሊላ ሰዎች ወደ ሰማይ አሻቅበው ጌታቸው ወደ ሰማይ ሲያርግ በእንባ በተሞሉ ዓይኖቻቸው ሲከታተሉ የሚወዱት አዳኛቸው ትዝታ ተራ በተራ በአእምሮአቸው ውስጥ ሳይመላለስ አልቀረም። ጴጥሮስ ጌታውን ሶስት ጊዜ እንዴት አድርጎ እንደካደው ታወሰው። የሱስም «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ትወደኛለህን?» ብሎ ሶስት ጊዜ የጠየቀው ጥያቄ በጆሮው ይደውልበት ጀመር። የተወደደው ሐዋርያ ዮሐንስም በጌታው ደረት ላይ ተደግፎ የዘላለም ሕይወትን ቃል ሲሰማ ትዝ አለው። ቶማስም ጣቶቹን በየሱስ ቁስል ውስጥ ሲከትና በእውነት ከሞት የተነሳው ረቡኒ እንደሆነ ለማረጋገጥ የሞከረው ታወሰው። መግደላዊት ማርያምም ፈሪሳውያን በድንጋይ ሊወግሩአት ከበዋት ሳሉ በጌታ እግር ስር ተደፍታ ስታለቅስ ስዕሉ እንደገና ቦግ ብሎ ታያት። የሱስም «ፈራጆችሽ የታሉ? እኔም አልፈርድብሽም ተነሺና ሂጂ ዳግመኛም ኃጢአት አትሥሪ» ብሎ በምህረት ቃሉ የቆሰለውን ልብዋን የፈወሰውን አሰበች። አልአዛርም ጌታ ከሞት አስነስቶ አዲስ ሕይወት እንዴት እንደሰጠው በምስጋና ልብ ትዝ አለው።

ደቀመዛሙርቱም ጌታቸው ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ። «የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመለሳል» አሏቸው። በዚያን ጊዜ የሃዘን ስዕል በተሳለባቸው ፊቶች ላይ የተስፋ ነጸብራቅ ዳግም ቦግ ብሎ በራ። «ይመለሳል» የሚለው ቃል እንደ መልካም ዜማ በአእምሮአቸው ያስተጋባ ጀመር። የምጽዓቱ ተስፋ እንደሚቀጣጠል እሳት በልቦቻቸው ውስጥ ተያያዘ። ከዚህን እለት ጀምሮ ይህ መዝሙራቸው እና ስብከታቸው ሆነ። ሰላምታቸው እና መላው ሕይወታቸው በምጽአቱ ተስፋ በ «ማራናታ» (ጌታ ይመጣል) አማረ።

አጽናኙ መንፈስ ቅዱስም በበዓለ አምሳ ቀን በታላቅ ኃይል በደቀመዛሙርቱ ላይ ከወረደበት ጊዜ ጀምሮ ስለ ናዝሬቱ የሱስ የሚሰጡት ምስክርነት የመስቀሉን ኃይል ለአህዛብ ሁሉ የሚያበስር ሆነ። «የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ቃል ስሙ። ራሳችሁ እንደምታውቁ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበር። እርሱንም



በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው ተሰጥቶ በአመጸኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሳው። ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና» (ሐዋ 2፣22-24)

የሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ለተከታዮቹ የተናገራቸው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ይታወሳቸው ጀመር። «ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ እንዲያስ ባይሆን ባልሁዋችሁ ነበር ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጀሁላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።» (ዮሐ 14፣1-3) ይህ ቃል በዚህች ምድር ላይ እንግዶችና መጻተኞች እንደሆኑ ዘወትር የሚያሳስባቸው መመሪያ ሆናላቸው። ስለዚህ መዝገባቸውን ሌባ በማይሰርቅበትና ብል በማይበላበት መሰብሰብ እንደሚገባቸው ተገነዘቡ። ልባቸው በምታምረው የተስፋ ምድር በፍቅር ተያዘ። «አንዳንዶቹ ስለ ወንጌል ብለው እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ ፣ ሌሎቹም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወህኒ

(በገጽ 2 ይቀጥላል)

በዚህ እትም ውስጥ


| | |
|---|---|
| የምጽአቱ ተስፋ | 1 |
| ከአዘጋጆች | 2 |
| ከአንባቢዎች | 2 |
| የፈቃደኛ ወንጌላውያን እንቅስቃሴ - (1) | 3 |
| ጉንፋንን እንዴት መከላከል እችላለሁ? | 4 |
| የሱስ - የራእይ መጽሐፍ አብይ ተዋናይ | 5 |
| የትንቢት ስጦታ በመጨረሻው ዘመን | 6 |
| ለሚታመኑበት ሁሉ ኃይሉን ያስታጥቃቸዋል | 7 |
| የሃይማኖቱ ዓለም ወቅታዊ ዜናዎች | 7 |
| «የተስፋ ድምጽ» ዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ | 8 |
| የጥያቄዎ መልስ | 8 |


Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# ከአዘጋጆች



# ወንጌል የምጽአቱ . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

### *የተወደዱ አንባቢ ሆይ!*

በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሰር ሼልተን ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ወደ ደቡብ ዋልታ ለመድረስ መንገድ ጀመሩ። ነገር ግን ወደ ግባቸው ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው መርከባቸው በበረዶ ተይዛባቸው ታላቅ ጉዳት ደረሰባት። በሕይወት ለመትረፍ ያለው ዕድልም በሌሎች ትናንሽ መርከቦች ላይ መሳፈርና ወደ ደረቅ ምድር ለመድረስ መሞከር ነበር። ቢሆንም ግን እነዚህ ትናንሽ መርከቦች ጭነት ስለበዛባቸው ይህም ሙከራ ብዙ ተስፋ ያለው ሁኖ አልተገኘም። ስለዚህ የመርከቢቷ ካፒቴይን ከዚህ የሚከተለውን እርምጃ ለመውሰድ ቆረጡ፥- ከሥራ ባልደረባዎቻቸው ውስጥ ግሚሱን በቅርብ ባለች አንዲት ደሴት ላይ ትተው እርሳቸው ግን ከሌሎቹ ጋር ደረቅ መሬት ፍለጋ ሙከራ ለማድረግ ተነሱ። በደሴቷ ለተውዋቸው ሰዎችም «እዚሁ ጠብቁኝ! ወደ ደረቅ ምድር እንደደረስኩ ሌላ መርከብ ይዤ እመጣና እወስዳችኋለሁ» ብለው በባልደረቦቻቸው ልቦች ውስጥ የሚቀር የተስፋን ጭላንጭል እንደዘሩ በብቸኝነትና በብርድ መሃል ትተዋቸው ሄዱ። ካፒቴይኑና አብረዋቸው የሄዱቱ ሰዎች ከታላቅ ችግር በኋላ ወደ ደረቅ ምድር ደረሱ።

ትተዋቸው የመጡትንም ሰዎች ተመልሰው ለመውሰድ በመጀመሪያ መርከብና ረዳቶች መፈለግ ስለነበረባቸው ብዙ ጊዜ ፈጀባቸው። በተጨማሪም መጥፎው የአየር ሁኔታም ጉዞአቸውን ቶሎ እንዳይጀምሩ እንቅፋት ሆነባቸው። በዚህ መልኩ ብዙ ሳምንታትና ወራት አለፉ። በመጨረሻም ዝግጅቱ ሁሉ አልቆ ካፒቴይኑና ረዳቶቻቸው ትተዋቸው የመጡትን ጓደኞቻቸውን ለመውሰድ መንገዱን ተያያዙት። «ለመሆኑ ባልንጀሮቼ በሕይወት ይኖሩ ይሆንን?» የሚለውን ጥያቄ በአእምሮአቸው እያሰላሰሉ ወደ ደሴቲቱ የሚደርሱበትን ቀን በጉጉት ይጠባበቁ ጀመር። በመጨረሻም ወደ ደሴቱቱ ሲደርሱ የነበረው ደስታ ይህ ነው የሚባል አልነበረም። ጓደኞቻቸው በሙሉ በሕይወት መቆየት ብቻ ሳይሆን የአካላቸውና የመንፈሳቸው ጤንነት በጣም ጥሩ ሁኔታ ላይ ሁኖ አገኙት። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? እነዚህስ ሰዎች በዚህ በብቸኝነትና ከባድ ጊዜ ምን አግኝተው ይሆን?

በደሴቱ ከቀሩት መሃል ሌሎቹን የሚያነቃቃና የሚያበረታታ አንድ ሰው ነበር። ሰዎቹ ተስፋ ቆርጠውና አዝነው ሲያያቸው «ታገሡ! ጸንታችሁ ቆዩ! ካፒቴይኑ ሊወስደን በርግጥ ይመለሳል። ቃል ገብቶልናል። ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ! ምናልባትም የሚመጣው ዛሬ ይሆናልና» እያለ ዘወትር ይነግራቸው ነበር። ይህም ባልንጀሮቹ ሁሉ «እመለሳለሁ» ያለውን ካፒቴይን ከእለት ወደ እለት በተስፋ እንዲጠብቁት ረዳቸው።

የተወደዱ አንባቢ ሆይ! የትንቢት ቃልም ሊመጣ ያለውን የክብር ንጉሥ ለመቀበል እንዲዘጋጁ ልታበረታታዎ ትፈልጋለች። የሱስ «ወደ እኔ ልወስዳችሁ ሁለተኛ እመጣለሁ» ብሎአል። በርግጥም ይመለሳል! ማራናታ!

*ዳዊት መሐሪ እና ዳዊት መንግሥቱ*

ተፈተኑ፣ በድንጋይም ተወግረው ሞቱ፣ ተፈተኑ፣ በመጋዝ ተሰነጠቁ፣ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ። ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ። ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ» (ዕብራ 11፣36-37)። በዚህ ሁሉ ውስጥ በራሱ በክርስቶስና አስቀድሞም በነቢያት የተነገረው የዳግም ምጽአቱ የትንቢት ቃል ከጊዜ ወደ ጊዜ እያስተጋባ መጣ። የክርስቲያን ሰማእታት ደም በፈሰሰ ቁጥር የወንጌል እሳት የበለጠ ተቀጣጠለ። ለሰማእታትና እግዚአብሔርን ለሚፈሩ የመታሰቢያ መጽሐፍ ተጻፈላቸው፥- «የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈሩ እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ፣እግዚአብሔርም አደመጠ ሰማም፤እግዚአብሔርንም ለሚፈሩ የመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ ተጻፈ» (ሚልክ 3፣16) የሱስም አለ «ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ»። ደቀመዛሙርቱ ይህንን ቃል ከጌታቸው አፍ ሲወጣ ሲሰሙ በእምነት ክንፎች አስቀድመው ወደ ሰማይ መንግሥት ገቡ። «ወደምሄድበት ታውቃላችሁ መንገዱንም ታውቃላችሁ» ብሎ የማበረታቻ ቃል ሲናገርም ተጠራጣሪው ቶማስ «ጌታ ሆይ! ወደምትሄድበት አናውቅም እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን?» አለው። የሱስም «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ» ሲል መለሰለት። አዎን ይህ መንገድ እውነትና ሕይወት የሆነው ጌታ ሁለተኛ ይመጣል። ይህ ጌታ ወዳጆቹን ወደ ሰማይ ቤቱ ለመውሰድ ይመለሳል።

በማቴዎስ ምእራፍ 24 ቁጥር 3 ላይ ስናነብ ደቀመዛሙርቱ የሱስ በደብረ ዘይት ለብቻቸው ተቀምጦ ሳለ ወደ እርሱ ቀርበው «ለመሆኑ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድን ነው?» ብለው ጠየቁት። የሱስም ከላይ በተጠቀሰው ምእራፍ ውስጥ ያሉትን ምልክቶች ነገራቸው። በመቀጠልም በቁጥር 44 ላይ «ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፤የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና» ሲል አሳሰባቸው። የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ የሆነው የሱስ ዳግመኛ በክብር ሲመጣ የእግዚአብሔርን ወዳጆች ወደዘላለም ቤታቸው ይወስዳቸዋል። ያን ጊዜ ስንብት የሚባል ነገር አይኖርም። ያን ጊዜ እንግድነትና መጻተኛነት ይቀራል። ያንጊዜ የዘላለም ደጆች ተከፍተው በበጉ ደም የታጠቡትን ከምድር የተዋጁትን ያስገባሉ። ያንጊዜ አዳኙን ፊት ለፊት እናየዋለን። ያንጊዜ ሞት ከመሀከላችን መንጭቆ የወሰዳቸው ሙታን ከመቃብሮቻቸው ይወጣሉ። ያንጊዜ ጌታ ራሱ በእነዚያ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ በተቸነከሩት መዳፎቹ እንባችንን ያብሳል። «ቅዲስቲቱዋ ኢየሩሳሌም ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። ታላቅም ድምጽ ከሰማይ እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው። ከእነርሱም ጋር ያድራል እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሁኖ አምላካቸው ይሆናልና እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል ሞትም ከእንግዲህ አይሆንም ሃዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ስቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም የቀደመው ስርአት አልፎአልና» ብሎ ሲናገር ሰማሁ (ራእይ 21፣3-4)

የተወደዱ አንባቢ ሆይ! በምድር ላይ የሚኖር ሰው እርስዎ ብቻ ቢሆኑ ኑሮ የሱስ ለእርስዎ ብቻ ብሎ የሰማይ መንግሥቱን ለቆ ወደዚህች ምድር መጥቶ ስለ ኃጢአትዎ ይሞት ነበር። ከዚያም ለእርስዎ ብቻ ብሎ ዳግም ይመጣና ወደ ሰማይ ቤቱ ይወስድዎት ነበር። እርስዎ ለየሱስ በጣም ክቡርና የተለዩ ሰው ነዎት። በክርስቶስ ልብ ውስጥ የእርስዎን ቦታ የሚተካ ሌላ ማንም የለም። ይህ ነው አስደናቂው፣ቃላት የማይገኙለት የእግዚአብሔር ፍቅር!።

የጌታ ዳግም ምጽአትም ቅርብ እንደሆነ የዘመናት ሁሉ መጽሐፍ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት ቃል በማያጠራጥር መንገድ እንረዳለን። እርስዎስ አምላክዎን ለመገናኘት ተዘጋጅተዋል ወይ? እስከ አሁን ድረስ ሕይወትዎትን ለየሱስ አሳልፈው ካልሰጡ ይህንን መልእክት አንብበው እንደጨረሱ ውሳኔ ያድርጉ ዘንድ በጌታ ስም እጋብዝዎታለሁ። ወይንም ደግሞ ከክርስቶስ ጋር ጉዞ ጀምረው መሃል ላይ በተለያዩ ወጥመዶች ተጠላልፈው በተስፋ መቁረጥ መንገድ ላይ ካሉ ደግሞ ጌታ ልክ እንደ ቀድሞው እንደሚወድዎትና ከገቡበት አዘቅት ሊያወጣዎ በጉጉት ላይ እንዳለ ልገልጽልዎ እወዳለሁ። ስለዚህ «ጌታ ሆይ እባክህ እጄን ያዘኝ» ይበሉት። ምናልባት ደግሞ «እኔ ከሃዲ ነኝ። የእግዚአብሔርን መኖር እንኳን እጠራጠራለሁ» የሚሉም ከሆነ እስቲ በእውነት ልብ «ፈጣሪ ሆይ! ካለህ በፈቀድከው መንገድ ራስህን ግለጽልኝ» ብለው ይጠይቁት።

በውሳኔዎና በሚወስዱት እርምጃ ሁሉ መለኮታዊ ኃይል እንዲረዳዎ ፀሎቴ ነው◆

ዳዊት መንግሥቱ

## ከአንባቢዎች

ውድ የትንቢት ቃል አዘጋጆች ሆይ! መጽሄታችሁን በተከታታይ በማንበብ እጅግ ተባርኬበታለሁ። ጌታ ይባርካችሁ! ሥራችሁ ከሥራዎች ሁሉ ዘላቂ እና በእግዚአብሔር የተመሰገነ እንደሆነ ላሳስባችሁ እወዳለሁ። በተጨማሪ ደግሞ መጽሄታችሁ በአየር (በሰማይ) ለአለም ሕዝቦች ስትዳረስ በመጽሐፍ ቅዱሳችን የሶስቱ መላእክት በሰማይ መካከል የዘላለም ወንጌል ይዘው ሲበሩ ለዮሐንስ ታይተዋል። ስለዚህ እግዚአብሔር ይህንን መልእክት የሚያስተላልፍበት አንዱ መንገድ ስለሆነ በርቱ እላችኋለሁ። ውድ አንባቢያን ደግሞ እናንተም ይህንን በመረዳት በመጽሄቱ ተልእኮ በሚያስፈልገው ሁሉ ተባበሩ! ቾል አትበሉ እላለሁ።

*ወንድሙ ዴንሳ (ከወላይታ)*

ለላካችሁልኝ የትንቢት ቃል መጽሄት አመሰግናለሁ። አምላክ ጨምሮ ይባርካችሁ፥ራእያችሁን ያስፋላችሁ። በመጽሄትዋ እየተባረክሁ ስለሆነ በጣም ደስ ብሎኛል። ደግሞም የራእይን መጽሐፍ ለማስጠናት ስለጀመራችሁ አምላክ ይባርካችሁ። በሰማይ እስክንገናኝ ድረስ ጠንክሩ።

*አበባዬ ገብረእግዚአብሔር (ከአ.አ.)*

ከባህር ማዶ ሆናችሁ በአገራችን ላሉት ለኢትዮጵያውያን ለምታበራክቱት የወንጌል ተልእኮ ጌታ ይባርካችሁ ስል እጅግም ከልቤ ነው። የትንቢት ቃል የምትለው መጽሄታችሁ እጅግ ልብን

*የምታድስ ናት፣በርቱ።ታደሰ አዱኛ (ከአምቦ)*

ሥራችሁን ከእግዚአብሔር ጋር ስለምትሰሩ ምንም ችግር እንደማይደርስባችሁ እተማመናለሁ። የእግዚአብሔር ሰላምና ደስታ አእምሮአችሁን ይሙላ። መንፈሳዊ ጽሁፎችን ማንበብ ከምንም ነገር በላይ ያስደስተኛል። «ፓሩሲያ» የሚለውን የፍልውሃ አድቬንቲስት ቤ/ክ የምታሳትመውን መጽሄት ከጓደኛዬ አብርሃም ጋር ስናጠና የእናንተን አድራሻ አገኘን፤ደስም አለን፤ልንጽፍላችሁም በቃን። እኔም ጓደኛዬም የትንቢት ቃል መጽሄት ተጠቃሚ በመሆንና በረከቱን ለመቋደስ እንፈልጋለን። ስለዚህ መጽሄታችሁን አደራ ላኩልን።

*አሳቡ ሃንካም (ከአዋሳ)*

(በገጽ 4 ይቀጥላል)



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# የፈቃደኛ ወንጌላውያን እንቅስቃሴ - *ክፍል አንድ*

## ወንጌል በኢትዮጵያ

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የሚገኙ የአድቬንቲስት ምእመናን በፈቃደኝነት በመነሳሳት ብዙ የወንጌል እንቅስቃሴን በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ይህም «በመጨረሻ ሥራውን የሚጨርሱት ምእመን» መሆናቸውን የሚጠቅሰውን «የትንቢት መንፈስ» መልእክት ሳስታውስ በእርግጥም ደህንነታችን እጅግ መቅረቡን ያስገነዝበኛል። በመሠረቱ ይህ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ቆየት ብሎአል። አንዴ ሲበራ መልሶ ሲደክም እንደምንም ብሎ ከዛሬ ቀን ደርሶአል።

ባለፈው አመት የተወሰንን ምእመን ሆነን ገንዘብ አዋጣንና የጥንት አድቬንቲስቶች መንደር ወደ ሆነው ዛሬ ግን ፈጽሞ ወደ ደከመው ወደ ደብረ ታቦር አሞራ ገደል ኮንፈረንስ ለማድረግ ሄድን። ጌታም አገልግሎታችንን ባረከው። ሕዝባችንን እንደገና አሰበ። በዚያም ቦታ ከፍተኛ የሆነ ተሃድሶና መነቃቃት ሆነ። እንዲያውም ሰይጣን ይህን ለማደናቀፍ ብዙ ሲጥር ሳይሳካለት ሲቀር በመጨረሻ እህላችንን ይዛ የምትመጣ መኪና እንድትበላሽ አደረገ። በሌላ ትራንስፖርት እንዳይመጣ ጊዜው የግዳጅ ጊዜ ነበርና (የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት ነበር) ምንም የመጓጓዣ ዘዴ አልነበረም። ምእመናንም በልዩ ልዩ ተአምራዊ መንገድ ነበር የመጡት። በዚህን ጊዜ የነበረን እድል (ያለ እቅዳችን) ከአካባቢው በሬ ገዝተን ማረድ ነበር። በሬው ተገዝቶ በሚታረድበት ጊዜ ወዲያው ሰዎች መጡና «ኑ ተአምር እዩ» አሉን። «ምንድን ነው?» ብለን ስንሄድ ከበሬው አሞት ከረጢት ውስጥ ወርቅ ተገኘ። በጣም ደነቀን። ጌታ ወጪያችንን ለመሸፈን ከጎናችን እንደቆመና አገልግሎታችንንም እንደወደደው ተሰማን። ወርቁም ተሸጦ የበሬውን ዋጋ ቻለ። ከዚህ በኋላ ይህን ምስክርነት ለወገኖች ሁሉ ስንነግር ሁሉም ለአገልግሎት ተነሳሱ። ከውጭም ከአገር ውስጥም የእርዳታ እጃቸውን መዘርጋት ጀመሩ። እኛም አገልግሎታችንን በሰፊው ተያያዝነው። ጌታ በብዙ ባረከን። ምእመንም በየቦታው ተነቃቁ ተበረታቱ።

### የዘላለም ወንጌል ለአዲስ አበባ

ከዚህ በኋላ ከእንግዲህ ደግሞ ለየት ያለ የወንጌል ጥረት በማድረግ ይህን የመጨረሻ የዘላለም ወንጌል ለሰው ሁሉ ማድረስ አለብን ብለን እርስ በእርስ ተነጋገርን። ከዚያም በፍልውሃ አድቬንቲስት ቤ/ክ የምንገኝ ፈቃደኛ ወንጌላውያን በሲስተር ኢትዮጵያ ታደሰ መሪነት ይህን ጥረት በአዲስ አበባ ለማድረግ ወሰንን። በመጀመሪያ ብትን ጽሁፎችን አሳትመን ወደ 30 ሺ ኮፒ አባዛንና ማሰራጨት ጀመርን። የሕዝቡን የወንጌል መጠማት ስናይ እንግዲያውስ ትልቅ የወንጌል ጥረት ማድረግ ይኖርብናል አልንና አቀድን። በጀቱንም አወጣንና መንቀሳቀስ ጀመርን። መጀመሪያ ስናቅድ 40 ሺ ብር ብናሰባስብ ብለን ስንነሳ ብዙዎቹ «ይህ ሁሉ ገንዘብ ከየት ይመጣል?» ብለው ተስፋ ቆረጡ። «ግድ የለም ጌታ ያመጣዋል» ብለን ተነሳሳን። እንቅስቃሴው እየተጠናከረ መጣ። ልዩ የተሀድሶና የመነቃቃት ቀናትን አደረግን። ከዚያም ምእመኑ መንቀሳቀስ፣ገንዘብም መግባት ጀመረ። አንድ ቤተሰብ 20ሺ ሌላው 10ሺ ሰጡ። 5ሺ, 4ሺ, 3ሺ የሚሰጡም ብዙ ነበሩ። በአሜሪካ ያሉ አንዳንድ ወዳጆችም በገንዘብ ተባበሩን። የወንጌል ጥረቱ ከመጀመሩ ከሳምንት በፊት በጀቱ 100ሺ ብር ደርሶ ነበር።

አሁን የእኛም ራእይ እየሰፋ መጣ እቅዳችንን አሰፋን። ብዙ የሚታተሙ ጽሁፎችን በተለይ በአሁኑ ጊዜ የሚነሱትን ጥያቄዎች የሚፈቱ «ሰንበትና ጸጋ እንዲሁም የሕግን ትርጉም በተመለከተ ዝርዝር መግለጫ የሚሰጡትን በፓስተር ታምሬ አባተ የተዘጋጁት ትራክቶች ታተሙ። ከዚያም ለወንጌል ጥረት መጋበዣ የሚሆኑ የጥሪ ወረቀቶች ወደ 8ሺ ኮፒ ተባዝተው ተሰራጩ። በየስልክ እንጨቱና በየአጥሩ የሚለጠፉም ተዘጋጅተው ተለጥፈዋል። በሬዲዮ በጋዜጣና በቴሌቪዝን ማስታወቂያ ተነገረ። በአሁኑ ጊዜ አዲስ አበባን የመንፈስ ቅዱስ ጥሪ እያዋከባት ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም። ጥሪውን ያላየና ያልሰማ ነፍስ የለም። እኛም በ24 ሰአት የጸሎት ሰንሰለት ውስጥ ሆነን ነገራችንን ለጌታ አቀረብን። በፍልውሃ አድቬንቲስት ቤ/ክ ግቢ ወስጥ ያለው ሸርጉድ መአዛው ልዩ ነው። «በዚሁ ስራው አልቆ ወደ ሰማይ» የሚያሰኝ ነው። የዚህን ታላቅ የወንጌል ጥረት ውጤት ለሚቀጥለው እትም ይዤ እቀርባለሁ።

### ወንጌል በያቤሎ

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ መልካም ሥራ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ምእመናን ሁሉ እየተጋባ ነው። በየቦታው የጌታን ሥራ ለመሥራት ሁሉም እየተነቃቃ ይገኛል። ጌታ በያቤሎ ስላደረገው ተአምር ልንገራችሁ፥ አንድ በሌላ ቤ/ክ የሚያመልክ ወንድም በእድሜ ሸምገል ያሉ አዛውንት ያገኝና «መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ ፈልጌ ነበር፣ምን ላድርግ?» ይላቸዋል። እሳቸውም «በደንብ የምታስተምር ቤ/ክ አለች ሲባል ሰምቼ 30 ዓመት ጠበቅሁ ግን ብቅ አላሉም ስለዚህ ተስፋ ቆርጬ ቀረሁ። ቢሆንም የመላላክ ትምህርት አድራሻ አለኝና እስኪ በዚህ ሞክር» ብለው ይነግሩታል። የሚገርመው ያ አድራሻ «የትንቢት ድምጽ» አድራሻ ነበር። ይህ ሰው ወዲያውኑ ይጽፍና ተከታታይ የትንቢት ድምጽ ትምህርቶችን ይከታተላል። በትምህርቱ ልቡ ከመነካቱ የተነሳ በጣም ያዝንና «ለምን ይህን ልዩ ትምህርት ይዛችሁ ቁጭ አላችሁ?» ይልና ይገረማል። ያንን ትምህርት እየተከታተለ መታገስ ያቅተዋል። ከዚያም ለሚስቱ «እኔ ከብቶቼን ሸጬ እየዞርኩኝ ወንጌልን እሰብካለሁ» ይላታል። እሷም «እሺ» ትለዋለች። ከዚያም እየዞረ ሲያስተምር ከ600 በላይ የሚሆኑ ሰዎችን የአድቬንቲስትን መልእክት እንዲቀበሉ ያደርጋል። አንድ ቀን ይህንን ወንድም ከአዲስ አበባ ወንድሞች ሄደው ጎበኙት። በእርግጥም እውነት ነበር። ግን እነዚያን ሰዎች ሁሉ ለማጥመቅ በአካባቢው ለ3 ዓመት ድርቅ ስለነበር ማጥመቂያ ውሃ አልነበረም፣መሰብሰቢያም ቤ/ክ የለም። ሁሉም በዛፍ ስር ነበር የሚሰበሰቡት። ይህ በእንዲህ እንዳለ በእንግሊዝ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ለተራቡ ወገኖች እንዲሰጥ በማሰብ ብር አዋጡና «በቀጥታ ወደሚፈለገው ቦታ ሄዳችሁ ስጡ» ብለው ላኩልን። እኛም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ወደ ያቤሎ እርዳታውን ይዘን ሄድን። በዚያም እነዚህን ወገኖች ለመጎብኘት እድል አገኘሁ። የደቡብ ሰበካ በጀት በቂ ስላልነበረ ለእነዚህ ሰዎች የሚያስፈልገውን እርዳታ ማድረግ አልተቻለም ነበር።እንኳን ለነሱ አዲስ ቤ/ክ መክፈት ይቅርና ያለውንም ለመዝጋት የደረሰ ነው። ከአሁን በፊት በዚያ አካባቢ ባለው ከተማ ውስጥ ያሉት ምእመናን ቤ/ክ የሚሆን ቤት እንዲከራዩ ብለን 2ሺ ብር አዋጥተን ልከንላቸው ነበርና ለጊዜው እዚያ ተጠልለው አገኘናቸው። እንደደረስን እንዴት እንደተቀበሉን ለመግለጽ ያቅተኛል። ክርስቶስ ከሰማይ የወረደ ያህል ነው የተቀበሉን። በዚያም ሌትና ቀን እረፍት እስክናጣ ድረስ ጥያቄያቸውን ስንመልስ ስናስተምርና ስንጸልይ ሰነበትን። በከተማው የሚገኙ የሌላ ቤ/ክ አባላትም በድብቅ እየመጡ አብረው ሲሳተፉ ሰነበቱ። ከዚያም የእርዳታውን ፕሮግራም እንደጨረስን ወደ አዲስ አበባ ተመለስን። ያየሁትን አሳዛኝ ሁኔታ ለፈቃደኛ ወንጌላውያን አጫወትኳቸው። እንባ በእንባ ተራጨን። እኛ በሞቀ ቤ/ክ ስንት እውቀት ባላቸው ቀሳውስት እየተገለገልን ተቀምጠን ሌሎች ግን በእንዲህ አይነት ስቃይ አሉ የሚለው ሁሉንም አሳዘነው። ወዲያው ሁላችንም ቃል ኪዳን ገባን። ከዛሬ ጀምሮ ለዚያ ቦታ ልዩ መዋጮ እናደርጋለን፤ሄደንም ጭቃ አቡክተን ቤ/ክ ሰርተን እንመጣለን ብለን ተማማልን። ወዲያው 281 ብር ተሰብስቦ ሁሉም ይህን ሸክም ይዞ ወደየቤቱ ሄደ።



### አስደናቂው ተአምር

ሁሉም ይህንን የጸሎት አደራ ይዞ ወደ ጌታ መጮህ ጀመረ። የሚገርመው ይህ በሆነ በአምስተኛው ቀን የሚከተለው ተአምር ተፈጸመ። አንዲት እህት በመንገድ ስትሄድ አንዲት ሴት ታገኛትና «አውቅሻለሁ» ትላታለች። ይህችም እህት ደንገጥ ትልና «ምናልባት ፍልውሃ አድቬንቲስት ቤ/ክ ይሆን የምታውቂኝ?» ትላታለች። ሴትዮዋም «እዚያ አይደለም ግን አውቅሻለሁ» ትላታለች። አሁንም በዚህን ጊዜ ይህች እህት ቦርሳዋን ትከፍትና ብትን ጽሁፍ (ትራክት) ትሰጣታለች። ሴትዮዋም እነዚህን ጽሁፎች ትቀበልና ስለአድቬንቲስት እምነት አንዳንድ ጥያቄ መጠየቅ ትጀምራለች። ውይይቱም በመቀጠል «ለመሆኑ አድቬንቲስቶች ስንት ናችሁ?» ትልና ትጠያቃለች። እህታችንም «ብዙ ነን» ትላታለች። ቀጥላም «ስንት ቤ/ክ አላችሁ?» ስትላት «ቁጥሩን አላውቀውም ግን ብዙ ነው» ትላትና ቀጠል በማድረግ «ቢሆንም ግን ቤ/ክ የሌላቸው በዛፍ ስር የሚያመልኩ አሉ» በማለት ትናገራለች። ሴትዮዋም «በእርግጥ እንደዚህ በዛፍ ስር የሚያመልኩ አሉ?» በማለት ትጠይቃታለች። «አዎን» ትላለች እህታችን (በነገራችን ላይ ይህች እህት አዳነች አማረ ትባላለች)። «ድርጅቱ ለምን አይሠራላቸውም?» ትላለች እንግዳዋ ሴት። «ድርጅቱማ የገንዘብ እጥረት አለበት» ትላለች እህት አዳነች። በዚህን ጊዜ ይህች ሴት ቦርሳዋን ከፈት ታደርግና 5ሺ ብር

(በገጽ 2 ይቀጥላል)



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com



# ጤናችን

# ጉንፋንን እንዴት መከላከል እችላለሁ?

ቻርለስ ቶማስ "The Journal of Health and Healing" በሚለው መጽሄት ላይ ሲጽፍ እንዲህ አለ፥ «ከብዙ አመታት በፊት ህንድ አገርን ለቅቄ ወደ ሰሜን አሜሪካ ስመጣ ብዙ ጊዜ ጉንፋን ያጠቃኝ ጀመር። በአመት ውስጥ ከስድስት እስከ ስምንት ጊዜ ያህል ጉንፋን ይይዘኛል። ካመመኝ ደግሞ በደንብ ነው የሚያመኝ! ትኩሳቴ ይጨምራል፣ብዙ ከመናፈጥ የተነሳ የአፍንጫዬ የውስጠኛው ክፍል ይቆስላል፣ሳል ያስቃየኛል። እውነት ለመናገር ይህ በሽታ በተነሳብኝ ቁጥር ኑሮዬ በሙሉ ይቃወስብኛል፤ኃይልም አጣለሁ። አሁን ግን እግዚአብሔር ይመስገን እየተመራሁበት ባለው አዲስ ያኗኗር ዘይቤ ጉንፋንን ድል መንሳት ችዬአለሁ»።

ቻርለስ ቶማስ ይሰቃይበት የነበረውን የጉንፋን በሽታ ድል እንዲነሳ የረዱት 7 የጤና መመሪያዎች ነበሩ። ለአንባቢዎቻችን ይጠቅማሉ በማለት የትንቢት ቃል እነዚህን ምክሮች በቅደም ተከተል ይዛ ቀርባለች።



1. ሁልጊዜ ቢያንስ ከእኩለ ለሊት በፊት 2 ሰዓት ቀድመህ ከተኛህ በሰውነትህ ውስጥ ያለው «የውስጥ ሰዓት» ለጤንነትህ ጥቅምን እንዲያመጣ ታደርገዋለህ። ሐኪሞች እንደሚናገሩት ለሰውነታችን ጠቃሚ የሆኑ ሆርሞኖች (hormone) መረጨት የሚጀምሩት በሌሊት ነው። እነዚህ በተለይ ከእኩለሌሊት በፊትና በኋላ ሰውነታችን የሚረጫቸው ሆርሞኖች ጡንቻቻችን፣አጥንቶቻችን እና ነርቮቻችን እንዲታደሱና እንዲጠነክሩ ይረዳሉ። እግዚአብሔር ያለምክንያት ቀንንና ሌሊትን አልለየም። ስለዚህ በቂ የሌሊት እንቅልፍ ማግኘታችን ለጤናችን አስፈላጊ ነው።



2. ጠዋት ከእንቅልፍ እንደተነሳህ 2 ብርጭቆ ውሃ ጠጣ። በተለይ በክረምት ወቅት የምንተኛባቸው ክፍሎች ስለሚቀዘቅዙና በቤት ውስጥ ያለው አየር ስለሚደርቅ ሰውነታችን ፈሳሽን ይፈልጋል። በየቀኑ ብዙ ውሃ ጠጣ፤ሽንትህም ንጹህ ይሆናል። ሐኪሞች እንደሚመክሩት ከሆነ አንድ ሰው በቀን ከ6-8 ብርጭቆ ውሃ መጠጣት አለበት።

3. ገላህን በሙቅ ውሃ ከታጠብክ በኋላ መጨረሻ ላይ በቀዝቃዛ ውሃ ተለቃለቅ። ይህንን ባደረግህ ቁጥር «Lysozyme» የተባለው በተለይ በአፍና በአፍንጫ ውስጥ የሚገኘው ኤንዛይም (Enzyme) በሰውነትህ ውስጥ የበለጠ እንዲመነጭ ታደርገዋለህ። « Lysozyme» የጉንፋንን ቫይረሶች የመግደል ኃይል አለው።



4. በየጠዋቱ ከምትመገበው ጤናማ ቁርስ በተጨማሪ በየቀኑ ብርቱካን፣መንደሪን ወይም እንደዚያ የመሳሰሉትን ፍራፍሬዎች ብላ። በአርቴፊሻል መልክ ከተሠሩት መድሃኒቶች ይልቅ በእንደዚህ አይነት ፍራፍሬዎች ውስጥ ያሉት «Phytochemicals» እና «fiber» የበለጠ ጥቅም ይገኝባቸዋል።



5. በየቀኑ በተቻለ መጠን ከቤት ውጪ ስፖርት የምትሠራበት ጊዜ ይኑርህ። የምታደርገው የአካል ልምምድ ደግሞ ደስ የሚያሰኝህና አየር በደንብ ወደውስጥ እንድትስብ የሚያደርግህ ይሁን (ለምሳሌ ቮሊ ቦል፣ሩጫ፣ፈጣን ያለ እርምጃ እና የመሳሰሉት)። የጓሮ አትክልት ሥራም ለሰውነትህ ጥሩ መሆን ብቻ ሳይሆን ትርፍም ያስገኝልሃል። እንደዚህ አይነት የአካል እንቅስቃሴዎች ለሳንባ ጤንነትና ለመላው አካል ታላቅ ጥቅም አላቸው።



6. በተቻለ መጠን «Stress» የሚያስከትሉ ነገሮችን ቀንስ። ምክንያቱም «Stress» በበዛብህ ቁጥር ሰውነትህ ለበሽታ የተጋለጠ ብቻ ሳይሆን በሽታዎችንም ለመከላከል ኃይል ያጥረዋል (ለምሳሌ ጉንፋንን)።



7. በየቀኑ የጥሞና ጊዜ ይኑርህ። ሥራህን ሁሉ ትተህ አምላክህን ለማመስገን ጊዜ ውሰድ። በሕይወትህ የሚያደርጋቸውን መልካም ነገሮች ሁሉ እያስታወስክ እግዚአብሔርን አመስግን፣አወድሰውም። ይህንን በምታዘወትርበት ጊዜ ሰላምንና እረፍትን ታገኛለህ። ይሄኛው «መድሃኒት» ከሌሎቹ ይልቅ የተሟላ ጤንነት እንዲኖርህ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤ከበሽታዎችም ይከላከልልሃል። በሽታንም ለመፈወስ ድንቅ የሆነ መንገድ ነው።

የወንድም ቻርለስ ቶማስን ምክር በተግባር ማዋል እንድንችል ለሁላችንም እግዚአብሔር ፀጋውን ያብዛልን። ◆

---

## *የፈቃደኛ ወንጌላውያን . . .*

*(ከገጽ 3 የዞረ)*

እንደታሸገ «በዩ ቤ/ክ ለሌላቸው መስሪያ ይሁን» ብላ ትሰጣታለች።

እህት አዳነች በሶስተኛው ቀን ይህን ብር ይዛ ወደዚያ ፈቃደኛ ገሩፕ መጥታ ስትመሰክር የነበረውን ደስታ ልገልጸው አልችልም። በነገራችን ላይ ሴትዮዋ ስምዋንና አድራሻዋን አልናገርም ብላለች። «ደረሰኝ እንዴት ላምጣልሽ?» ስትላት «ሰኞ እዚህ ቦታ በዚህን ሰዓት ይዘሽ ነይ» አለቻት። በዚያን እለት እኔና እህት አዳነች ደረሰኙን ይዘን በተሰጠን የቀጠሮ ሰዓት እዚያ ቦታ ሄድን። በዚያም ከአንድ ሰአት በላይ ቆመን ማንም አልነበረም። እንግዲህ እንጃ ምናልባት መልአክ ይሆንን??!! እኛ ሁላችን እምነታችን «መልአክ» ነው ብለን ነው። ከዚያ ለያቤሎ 5281 ብር ሆነ። ከዚያም በየቀኑ አንድ ሺ ብር ወይም 200 ወይም 100 ብር እያለ ሲያድግ ይኸው ወር ሊሆነው ነው ከ8000 ብር በላይ ደርሶአል። ይህ ብቻ አይደለም የጋብቻ የወርቅ ቀለበታቸውን የሰጡ ፣ ሁለት ቀለበት አንድ የእጅ ሰዓት አንድ ወደ 400 ብር የሚያወጣ ትልቅ ያልጋ ልብስ ገቢ ሆኖአል። በዛ ላይ ጸሎቱም በደንብ ቀጥሎአል። ይህ በዚህ እንዳለ ከያቤሎ ያሉ ወንድሞችና እህቶች ስልክ ይደውሉና «አዲስ አበባ ምን እያደረጋችሁ እንደሆነ አናውቅም፤እኛን ግን መንፈስ ቅዱስ እያናወጠን ነው። እውነትን የምታስተምር ቤ/ክ ተገኘች እያሉ ሰዎች ከሌላ ቤ/ክ እየመጡ ነው። ይህች የተከራየናት ትንሽ ቤት እየተጨናነቀች ነው» ይሉናል። በጣም የሚያስደንቅ ነው። በሐዋሪያት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ እንዳስታውስ አደረገኝ «ጌታ የሚድኑትን እለት እለት ይጨምር ነበር» ይላል (ሐዋ 2፣47)

እንግዲህ እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴ በፈቃደኛ ወንጌላውያን እየተካሄደ ይገኛል። ለያቤሎ ቤ/ክ ሥራም ሆነ የሌሎች አገልግሎቶች በረከት ተካፋይ መሆን የሚፈልጉ ሁሉ አሁንም አስተዋጽዖአቸውን በደስታ እንቀበላለን። በእኛ መልካምን ሥራ መሥራት የጀመረው አምላክ እስከ የሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንደሚፈጽመው አምናለሁ። አሜን! ◆

*እንየት ሰንደቅ (ከአዲስ አበባ)*

> **«የገሊላ አሣ አጥማጆችን የጠራው አምላክ አሁንም ሰዎችን ለአገልግሎት ይጠራል። በመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት እንዳደረገው ሁሉ አሁንም በእኛ አማካኝነት ኃይሉን ለመግለጽ ፈቃደኛ ነው። ክርስቶስን ለዓለም ለማበርከት ከሰማያዊ መልእክት ጋር አብረን እንድንሠራ ተጠርተናል»**
>
> የዘመናት ምኞት, ገጽ 294

## *ከአንባቢዎች*

*(ከገጽ 2 የዞረ)*

በትንቢት ቃል ፍጹም የማላውቃቸው ስሞች አያለሁ። ያም አዳዲስ ምናልባት በዚህ ምድር ሳይሆን በመንግሥተ ሰማያት የማገኛቸው እህቶችና ወንድሞች እንደሚኖሩኝ ያረጋግጥልኛል። ደግሞም ጥንት የማውቃቸውን ደጀኔ አበበን፥ልሳነ ጎሽሜን፥ሙሉ አረጋውን አገናኝቶኛል። ባሉበት ስፍራ የእውነትና የብርሃን ምስክር ሆነው በመቆማቸው ጌታን አመሰግነዋለሁ። ፊደሉ በጣም ጥቃቅን ከመሆኑ በስተቀር አሁን የደረሰኝ መጽሄት ግሩም ነው። ጸሃፊዎች እነ አታክልት ኢሳያስን፥ምስጋናው አረጋን እና ስምረት መሐሪን ሌሎቹንም ሁሉ አመሰግናለሁ። ስለሼክ ዘካሪያስ፥ስለአለቃ ሞትባይኖር፥ከእነርሱም ተያይዞ የተገፋው ብዙ የታሪክ እርግማት ያስፈልገዋል። ተስፋ አለኝ አንድ ቀን ፓ/ር ጥሩነህ ወ/ሥላሴና ፓ/ር ብርሃኑ ንጉሤ ታሪኩን በቅድመ ተከተል በሚገባ እንደሚጽፋልን። በመጨረሻ አንባቢዎች ሁሉ ይህን መጽሄት በጸሎት፥በገንዘብ፥የተለያዩ ጽሁፎችን በማቅረብ መርዳት አለብን። የክርስቶስ ወታደሮች ድካምን አያውቁም፣እንበርታ!።

*ግርማ ዳምጤ (ከአሜሪካ)*



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# የሱስ - የራእይ መጽሐፍ አብይ ተዋናይ



ተከታታይ ትምህርት

የራእይ መጽሐፍ ዋና ተዋናይ ስለሆነው የሱስ ብዙ የሚያስደንቁ እውነቶችን ይዞአል። ዛሬም የሱስን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የበለጠ ግልጽ በሆነ ብርሃን እናየዋለን። ውድ አንባቢ፥ ጥናቱን ከመጀመርዎ በፊት መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንዲገልጽልዎ ይጋብዙት።

1) የራእይ መጽሐፍ ክርስቶስን እንዴት ይገልጸዋል?
ራእይ 1፣13-16 እስከ እግሩ ድረስ ልብስ ለብሶአል ... በወርቅ መታጠቂያ ታጥቋል ... ራሱና የራሱ ጠጉርም እንደ ነጭ የበግ ጠጉር እንደበረዶም ነጭ ነበሩ ... ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ ... እግሮቹም በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር ... ድምፁም እንደ ብዙ ውሃዎች ድምፅ ነበር ... ፊቱም በኃይል እንደሚያበራ እንደ ፀሐይ ነበር።
(በተጨማሪም ትንቢተ ዳንኤል 10፣5-9 ያንብቡ። ዮሐንስም ሆነ ዳንኤል የሱስን በክብሩ ባዩት ጊዜ ዝለው መሬት ላይ ወደቁ)

2) የሱስ ለኛ ምን አደረገልን?
ራእይ 1፣5 «...ለወደደን ከኃጢያታችንም በደሙ ላጠበን ... ካህናት እንድንሆን ላደረገ ... »
(በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ይቀርቡ የነበሩት በካህናት በኩል ነበር። የሱስ ግን ይህንን ስርአት ቀየረው። እግዚአብሔርን በቀጥታ እንቀርበው ዘንድ ሁላችንንም ካህናት አደረገን። ይህ በጣም የሚያስደንቅ ነው!)

3) በራእይ ምእራፍ 5 መሠረት የሱስ ክብርና ምስጋና እንዲገባው ያደረገው ምንድን ነው?
ራእይ 5፣8,9,12 «...ታርደሃልና በደምህም ... ሰዎችን ዋጅተሃልና ...»
(«በግ» ወይም «ጠቦት» የሚለው ለየሱስ የተጠቀሰው ቃል በራእይ መጽሐፍ ውስጥ 26 ጊዜ ተጠቅሶአል። የሱስ በእርግጥ የእግዚአብሔር በግ ነው «ዮሐ 1፣29» በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሰዎች ኃጥያት ሲሰሩ ጠቦት ይሰዋ ነበር። እነዚህ ጠቦቶች የክርስቶስ ምሳሌ ነበሩ። እርሱ የዓለምን ሁሉ ኃጢያት ተሸክሞአልና። የእግዚአብሔር በግ የሱስ በእኛ ምትክ በቀራንዮ ላይ ሞተልን። በእርሱ በኩል ነጻነት ታውጆልናል። ስለዚህ ነው በራእይ ምእራፍ 5 ላይ ያሉት ሰዎች «የተሰዋው በግ ክብር ይገባዋል» ያሉት)

4) የየሱስ መስዋእትነት ኃጥያት ወደ ምድር ከገባ በኋላ ነው ወይስ ከመግባቱ በፊት የታቀደው?
1ጴጥ1፣18-20, ራእይ 13፣8, ኤፌ 1፣4 «ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ ...»

5) ራእይ ምእራፍ 4 እና 5 በተለይ በማህተም ስለተዘጋውና ማንም ሊከፍተው ስላልተቻለው መጽሐፍ ያንብቡ። በመጨረሻ መጽሐፉን የዘረጋውና ማህተሞቹን የፈታው ማን ነው?
ራእይ 5፣5-9 «ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ እርሱም የዳዊት ሥር ... » = የሱስ

6) ይህ ሊከፈት የተገባው መጽሐፍ ምን አይነት መጽሐፍ ነው?
መጽሐፉ ስም አልተሰጠውም። ግን ራእይ 5 ን በመመርኮዝ ከምድር ከተዋጁ ሰዎች ጋር የተያያዘ ነው። የራእይ መጽሐፍ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ስለ መጽሐፍ እና መጻሕፍት ይናገራል። እነሱም ከሰዎች ደህንነት ጋር የተያያዙ እንደሆኑም ያሳያል። ራእይ 3፣5 እና ራእይ 17፣8 ስለ «ሕይወት መጽሐፍ» ይናገራሉ። ራእይ 21፣27 «ለበጉ ስለሆነው የሕይወት መጽሐፍ» ይናገራል። ራእይ 20፣12 ላይ ደግሞ «መጽሐፍትም ተከፈቱ ሌላም መጽሐፍ ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው» ይላል።
(እነዚህ መጻሕፍት ሁሉ ከፍርድ ጋር የተያያዙ እንደሆኑ ያስተውሉ! ራእይ 13፣8 የዳኑቱ ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ እንደሚጻፍ ያሳያል። በራእይ 3፣5 መሠረት ደግሞ ከየሱስ ያፈገፈጉቱ ስማቸው ከዚህ መጽሐፍ እንደሚሰረዝ ይጠቅሳል)

7) የሱስ በሕይወት መኖር የጀመረው በድንግል ማርያም ከተወለደ ጀምሮ ነው ወይስ ከዚያ በፊት?
ራእይ 22፣6-7 « ... የነቢያትም መናፍስት ጌታ አምላክ ...»
(ራእይ 22፣6-7 የሱስን «የቅዱሳን ነቢያት ጌታና አምላክ» ነው ይለዋል። 1ጴጥ1፣10-11 ላይ የጥንት ነቢያትን የተናገረ ራሱ የሱስ እንደሆነ ያመለክታል። ሌሎች ብዙ ጥቅሶችም የሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት በሰማይ እንደነበር ይመሰክራሉ። ዮሐ 17፣5,24, ዮሐ 1፣1-3, ፊሊ. 2፣5-11 ይመልከቱ)

8) በፍጥረት ሥራ ላይ ማን ነበር ተካፋይነት የነበረው?
ራእይ 3፣14 «...በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው ...»
(«በመጀመሪያ» የሚለው በራእይ 3፣14 የተጠቀሰው ቃል ከአመጣጥ፣ከአጀማመር ጋር የተያያዘ ነው። Beck's የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንደሚያስቀምጠው «የእግዚአብሔር ተፈጥሮ መጀመሪያ» ይለዋል። የ Jerusalem መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ደግሞ «መሠረታዊ የሆነው የእግዚአብሔር ተፈጥሮ ምንጭ» ይለዋል። ሌሎች የሱስ ራሱ ፈጣሪ እንደሆነ የሚናገሩ ክፍሎችን ለማየት ኤፌ 3፣9, ዮሐ 1፣1-3,14, ዕብራ 1፣12, ቆላስያስ 1፣13-17 ይመልከቱ)

9) የሱስ ራሱ አምላክ ነውን?
አዎን። ራእይ 19፣13-16 እና ዮሐ 1፣1,14, ራእይ 22፣6-7 ይመልከቱ።
(በራእይ መጽሐፍ ወስጥ የሱስ «የእግዚአብሔር ቃል» ተብሎ ተጠርቶአል። በዮሐ 1፣1,14 ላይ ደግሞ ይህ «ቃል» ራሱ የሱስ እንደሆነና ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነም በጣም ግልጽ ያደርገዋል። ሌሎች ይህን ግልጽ የሚያደርጉ ቦታዎችን ይመልከቱ 1ጢሞ3፣16, ቲቶ 3፣4, ዕብራ 1፣8)



10) የሱስ ከመወለዱ ከ500 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር የሚመጣበትን ትክክለኛ ጊዜ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። ይህ ትንቢት በትክክል መፈጸሙ የሱስ እውነተኛው መሢሕ እንደሆነ ያረጋግጥልናል። ይህንን ትንቢት የት እናገኘዋለን?
ዳንኤል 9፣24-27 (ውድ አንባቢ ሆይ እነዚህን ጥቅሶች እርስዎ ያንብቡዋቸው)
(ይህ ትንቢት ለአይሁድ ሕዝብ 490 የምህረት ዓመታት እንደተሰጡት ያሳያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ሕግ መሠረት «አንድ የትንቢት ቀን አንድ ዓመት ነው» ሕዝ 4፣6። ይህም ማለት 70 ሳምንት ሲባዛ በ 7 ቀን 490 ቀናት ይሆናል። አንድ የትንቢት ቀን የሚያክለው አንድ ዓመት ስለሆነ 490 የትንቢት ቀናት 490 ዓመታት ናቸው ማለት ነው።)

11) ይህ 70 ሳምንት (490 ዓመት) የጀመረው መቼ ነው?
ዳንኤል 9፣25 «ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ ...»
(የእግዚአብሔር ሕዝቦች በፋርስ መንግሥት ግዞት ስር ነበሩ። አርጤክሰስ የተባለውን ንጉሥ አዋጅ እንዲያወጣ ጌታ አሳሰበው። በዚህም መሠረት ፈቃደኛ የሆኑ አይሁዶች በሙሉ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ከተማይቱን እንደገና ይገነቡ ዘንድ ፈቀደላቸው። ይህ አዋጅም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዕዝራ መጽሐፍ ምእራፍ 7 ተጠቅሷል።)

12) ይህ ትእዛዝ የወጣው መቼ ነበር?
ዕዝራ 7፣7,12,13 «በንጉሡ በአርጤክስስ በሰባተኛው ዓመት» (457 ከክርስቶስ በፊት)
(ዕዝራ ምእራፍ 7፣7,12,13 እንደሚያመለክተው ይህ አዋጅ የወጣው በንጉሥ አርጤክሰስ በሰባተኛው ዓመት ላይ ነው። ታሪክ እንደሚያመለክተውም ንጉሡ መግዛት የጀመረው በ464 ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። ስለዚህ ሰባተኛው ዓመት በ457 ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው። አዋጁ በሥራ ላይ የዋለው በዚህ በ7ኛው ዓመት ዕዝራ ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኋላ ነው።)

13) በዳንኤል 9፣25 መሠረት ንጉሡ አርጤክስስ ትእዛዙን ካወጣ ጀምሮ እስከ መሢሑ ድረስ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?
69 ሳምንት በ7 ሲባዛ (አንድ ሳምንት 7 ቀናት ነውና ያሉት) የሚሆነው 483 የትንቢት ቀናት ነው። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት መሠረት 483 ዓመታት ነው። በሂሳብ ሕግ መሠረትም በ457 ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምረን 483 ወደፊት ስንጓዝ የምንደርሰው 27 ዓ.ም. (ከክርስቶስ ልደት በኋላ) ላይ ነው።

14) ትንቢቱ እንደሚናገረው መሢሕ በ 27ኛው ዓ.ም. ማለትም ከ483 ዓመታት በኋላ ነው የመጣው?
አዎን፥ እነዚህን ጥቅሶች ያመሳክሩ፥ ሉቃ 3፣1,21,22, ሐዋ 10፣38, ዮሐ 1፣41
(«መሢሕ» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል «የተቀባ» ማለት ነው። «ክርስቶስ» ማለት ደግሞ በግሪክ ቋንቋ ይህንኑ አይነት ትርጉም አለው። የሱስ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ቢወለድም እስካልተቀባ ድረስ «የተቀባ» ወይም «መሢሕ» አልነበረም። የሐዋ ሥራ 10፣36 የሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንደተቀባ ይናገራል። በሉቃ 3፣21-22 የሱስን መሢሕ እንዲሆን ያደረገው የመንፈስ ቅዱስ ቅባት የተፈጸመው በተጠመቀ ጊዜ እንደሆነ ያሳየል። ሉቃ 3፣1 ደግሞ ጥምቀቱ የተፈጸመው በጢባሪዮስ ቄሳር 15ኛው


Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com



## የትንቢት መንፈስ

# የትንቢት ስጦታ በመጨረሻው ዘመን

ነቢያት በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ዘመን ትልቅ ሚና ይጫወቱ ነበር። በዘመናችንስ የትንቢት ስጦታ አስፈላጊነት ምን ያህል ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት ትንቢቶች ውጪ ሌላ ትንቢቶች ያስፈልጉናልን? ወይም ደግሞ ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ነብያት ብቻ ናቸውን ትንቢትን ይናገሩ የነበሩት ወይስ እስከ ምድር ታሪክ መጨረሻ ድረስ እግዚአብሔር ነቢያትን ያስነሳል? ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመስጠታችን በፊት የትንቢት ስጦታ ትርጉም ምን እንደሆነ እንግለጽ።

የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በጭንቀት ላይ ነበር። በጠላት ወታደሮች በመከበቡ ምክንያት የነበረበት ሁኔታ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሆኖ ሳለ «ኢዮሣፍጥ እግዚአብሔርን ሊፈልግ ፊቱን አቀና በይሁዳም ሁሉ ፆም አወጀ» (2ዜና20፣3) ሕዝቡም ከእግዚአብሔር ምህረትንና ድልን ለማግኘት ወደ ቤተ መቅደስ ለጸሎት ይጎርፉ ነበር። በጸሎትም ሰዓት ኢዮሣፍጥ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። ከደረሰበትም ችግር እንዲያወጣው ስለፈለገ እንዲህ ብሎ ጠየቀው፥ «አቤቱ የአባቶቻችን አምላክ ሆይ በሰማይ ያለህ አምላክ አንተ አይደለህምን? የአሕዛብንስ መንግሥታት ሁሉ የምትገዛ አንተ አይደለህምን? ኃይልና ችሎታ በእጅህ ነው ሊቋቋምህ የሚችል የለም» (ቁ.6) በመቀጠልም «አምላካችን ሆይ አንተ አትፈርድባቸውምን? ይህን የመጣብንን ታላቅ ወገን እንቃወም ዘንድ አንችልም፤የምናደርገውን አናውቅም ነገር ግን አይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው» (ቁ.12) ብሎ የምር ጸሎት ጸለየ።

በዚያን ጊዜ መላው ይሁዳ በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ሳሉ የሕዚኤል የሚባል አንድ ሰው ተነሳና በፍርሃት ይንቀጠቀጥ የነበረውን ሕዝብ አበረታታ፤እንዲህም አላቸው፥ «... ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው እንጂ የእናንተ አይደለምና አትፍሩ፣አትደንግጡም ... እናንተ በዚህ ሰልፍ የምትዋጉ አይደላችሁም . . . ተሰለፉ፣ ዝም ብላችሁ ቁሙ፣የሚሆነውንም የእግዚአብሔርን መድሃኒት እዩ፤እግዚአብሔርም ከእናንተ ጋር ነውና አትፍሩ፣አትደንግጡም...» (ቁ. 15-17) በነጋታውም ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ወታደሮቹን ለማበረታታት እንዲህ አለ፥ «...በአምላካችሁ በእግዚአብሔር እመኑ ትፀኑማላችሁ በነቢያቱም እመኑ ነገሩም ይሰላላችኋል» (ቁ.20)። ንጉሡ በነብዩ በየሕዚኤል ቃል ከመተማመኑ የተነሳ በጦርነቱ ላይ በግምባር ቀደምነት የታወቁትን ጀግና ወታደሮቹ በማድረግ ፈንታ የእግዚአብሔርን ክብርና ቅድስና ከፍ ከፍ የሚያደርጉትን መዘምራን እንዲቀድሙ አዘዘ። እነዚህም መዘምራን እምነት የሞላባቸውን መዝሙሮች በሚያሰሙበት ጊዜ እግዚአብሔር የይሁዳን ጠላቶች እርስ በእርሳቸው እንዲጨፋጨፉና አንዱ የራሱን ወገን እንዲገድል አደረገ። የታሪኩም መጨረሻ እንደሚነግረን፥ «... ያመለጠ ሰው አልነበረም» (ቁ.24)

### የትንቢት ስጦታ

በኢዮሣፍጥ ዘመን የሕዚኤል የእግዚአብሔር አፍ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ አባባል «ነብይ» ማለት ከእግዚአብሔር መልእክትን ተቀብሎ ለሕዝቡ የሚያስተላልፍ ሰው ማለት ነው። ነቢያት ትንቢት ይናገሩ የነበረው በራሳቸው ስልጣን ተነሳስተው አልነበረም «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» (2ጴጥ1፣21) በተጨማሪም ስለነቢያት በ1ሳሙ 9፣9 ላይ እንዲህ የሚል ጥቅስ እንገኛለን «ዛሬ ነቢይ የሚባለው ቀድሞ ባለ ራእይ ይባል ነበርና አስቀድሞ በእስራኤል ዘንድ ሰው እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ሲሄድ፥- ኑ ወደ ባለ ራእይ እንሂድ ይል ነበር» በዘመናት ሁሉ እግዚአብሔር በነቢያት አማካኝነት ነበር ፈቃዱን ይገልጽ የነበረው፥ «ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም» (አሞጽ 3፣7)

በአዲስ ኪዳንም ውስጥ የትንቢት ስጦታ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ በመሆን አስፈላጊውን ቦታ ይዞ እናገኘዋለን። (ሮሜ 12፣6, 1ቆሮ12፣28, ኤፌ 4፣11) ምእመናን በተለይ ይህንን ስጦታ ለማግኘት እንዲጥሩ ሐዋሪያው ዻውሎስ ይመክራል። በአዲስ ኪዳን ዘገባ መሠረት ነቢያት፥

1) ቤተክርስቲያንን በመገንባት ተካፋይነት ነበራቸው (ኤፌ 2፣20)

2) ቤ/ክ ወንጌልን እንድታስፋፋ ያደፋፍሯት ነበር (ሐዋ13፣1-2, ሐዋ 16፣6-10)

3) ቤተክርስቲያንን ያንጹ ነበር (1ቆሮ 14፣3-4, ኤፌ 4፣12)

4) ቤተክርስቲያንን ከሃሰት ትምህርት ይጠብቋት፣የምእመናንንም አንድነት ያጠነክሩ ነበር (ኤፌ 4፣14)

5) ምእመናንን ወደፊት ከሚደርሱባቸው ችግሮች ያስጠነቅቋቸው ነበር (ሐዋ 11፣27-30, ሐዋ 21፣4,10-14)

6) በቤ/ክ ውስጥ መሠረታዊ ትምህርቶችን በተመለከተ ክርክር ሲኖር እውነተኛውን ትምህርት ግልጽ ያደርጉ ነበር(ሐዋ 15፣32)

### የትንቢት ስጦታ በመጨረሻው ዘመን

ብዙ ክርስቲያኖች ከሐዋሪያት ዘመን በኋላ የትንቢት ስጦታ እንደሌለ ያምናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ቤ/ክ በመጨረሻው ዘመን በተለየ መንገድ የእግዚአብሔር አመራር እንደሚያስፈልጋት ይጠቅሳል። በመሆኑም የትንቢት ስጦታ ከሐዋሪያት ዘመንም በኋላ ትልቅ ሚና ይጫወታል። «እግዚአብሔር ለቤ/ክ የሰጠውን የትንቢት ስጦታ መልሶ ይወስደዋል» የሚል ጥቅስ በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አናገኝም። የትንቢት ስጦታ አላማውን እስካልፈጸመ ድረስ ሁልጊዜ ይኖራል። አላማውንም በኤፌ 4፣13 ላይ እናገኘዋለን፥ «...ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፤ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስ ሙላቱ ወደሚሆን ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ...»። ዛሬ ቤ/ክ የፍጽምናን ደረጃ ስላልደረሰች ሁሉም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች (የትንቢትንም ስጦታ ጨምሮ) የሱስ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ለእግዚአብሔር ሕዝብ አገልግሎት ሲባል በጥቅም ላይ ይውላሉ። «መንፈስን አታጥፉ፣ትንቢትን አትናቁ፣ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ» (1ተሰ 5፣19-20) እንዲሁም «...መንፈሳዊ ስጦታን ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ» (1ቆሮ 14፣1) ይላል ዻውሎስ ሲመክረን።

የትንቢት ስጦታን አስፈላጊነት ከተረዳን ዘንዳ «በዘመናችንስ ይህ ስጦታ በምን አይነት መልኩ እየተገለጸ ነው? ክርስቶስ ተመልሶ ከመምጣቱ በፊትስ ምን አይነት ሚና ይጫወታል?» ለሚሉት ጥያቄዎች በመጽሐፍ ቅዱስ የተመረኮዙ ሃሳቦችን ይዘን በሚቀጥለው እትማችን እንቀርባለን። ◆

ዳዊት መሐሪ

**_የሱስ - የራእይ መጽሐፍ . . ._**

*(ከገጽ 5 የዞረ)*

*ዓመት ላይ ነው ይላል። ታሪክም እንደሚያመለክተው የጢባሪዮስ 15ኛው ዓመት በ27ኛው ዓ.ም. ላይ ነው። ማለትም በትንቢት አስቀድሞ እንደተነገረው የሱስ በተጠመቀበት በዚያኑ አመት)*

15) የሱስ ከተጠመቀና በመንፈስ ቅዱስ ከተቀባ በኋለ ማስተማሩን ሲጀምር ይህ የዳንኤል ትንቢት ስለመፈጸሙ ራሱ ምን ተናገረ?

ማር 1፣14-15 «... <u>ዘመኑ ተፈጸመ</u> ...»

*(ይህ በጣም የሚያስደንቅ ነው! መሢሑ ከብዙ ዓመታት በፊት በነብዩ ዳንኤል በቀጥታ በተነገረው ትንቢት መሠረት በትክክለኛው ጊዜ መጣ። የሱስ በርግጥ መሢሕ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ይህ ሐቅ የማይናወጥና የምንቆምበት መሠረት ነው)*

16) በ70ዎቹ ዓመታት በመጨረሻው ሳምንት (7 ዓመት) መካከል ላይ ምን ይሆናል?

ዳን 9፣26-27 መሢሑ የሱስ በሳምንቱ መካከል «ይገደላል» ወይም ይሰቀላል።

*(በመጨረሻው ሳምንት መሃል ላይ የሱስ «ይቆረጣል» ይላል። የ7 ዓመታት ግማሽ 3 ዓመት ተኩል ነው። በ3 ዓመት ተኩል ላይ 27 ዓመታትን ስንደምር የምንደርሰው 31ኛው ዓመተ ምሕረት ላይ ነው። በዚህ ትንቢት በትክክል መፈጸም መሠረት የሱስ በርግጥ በፀደይ 31ኛ ዓ.ም. ላይ «ተቆረጠ» ወይም ተሰቀለ። የሱስም የእግዚአብሔር በግ ስለሆነና ምሳሌያዊ የሆነውን የጠቦቶችን መስዋእትነት በእውነተኛው መስዋእትነቱ በመስቀል ላይ ስለተካ «የዘወትር መስዋእት ይቀራል» ዳንኤል 12፣11። በተጨማሪም 1ቆሮ5፣7 ይመልከቱ)*

17) የሱስ በ 31ኛው ዓ.ም. ከተሰቀለ በኋላ ለአይሁዶች (በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ የነበሩት) የተሰጣቸው የምሕረት ጊዜ ምን ያህል ዓመት ነበር? መቼስ አለቀ?

ዳን 9፣24 በሰባው ዓመት መጨረሻ ላይ ለእስራኤል የተሰጠው የምሕረት ጊዜ ያልቃል። ይህም የሱስ ከተሰቀለ ከ ሶስት አመት ተኩል በኋላ መሆኑ ነው = በ34ኛው ዓ.ም.። በዚያን ጊዜ ለእስራኤል ሕዝብ የተሰጠው የምሕረት ዓመት ተፈጸመ። ወንጌልም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለአሕዛብ መሰበክ ተጀመረ።

18) ዛሬስ አይሁዶችም ሆኑ አሕዛብ እንዴት ነው የእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች የሚሆኑትና የሚድኑት?

ገላ 3፣29, ሮሜ 2፣28-29, ሮሜ 9፣6-8 «እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ <u>የአብርሃም ዘር</u> እንደተስፋውም ቃል <u>ወራሾች</u> ናችሁ»

*(ማንኛውም ሰው የሱስን የግል አዳኙ እንዲሆን ከወሰነ የእግዚአብሔር የተመረጠ ሕዝብ የመሆን መብት ተሰጥቶታል።)*

ውድ አንባቢ ሆይ እኛ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረን ብሎ የሱስ በመስቀል ሞተልን። ዛሬም በልባችን ደጃፍ ቆሞ እያንኳኳ ነው (ራእይ 3፣20)። ልብዎን ሊከፍቱለትና ሊያስገቡት ፈቃደኛ ነዎትን? ◆


Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# ለሚታመኑበት ሁሉ ኃይሉን ያስታጥቃቸዋል

## ምስክርነት



ኤሳው ወንድሙ በኩርነቱን አታልሎ በመውሰዱ ምክኒያት በያእቆብ ላይ ታላቅ ዛቻ ዛተበት። «አንገቱን ቆርጬ ለሰማይ ወፎች ምግብ አደርገዋለሁ» አለ። ያእቆብ ይህንን ታላቅ ቁጣ በሰማ ጊዜ ወደ በረሃ ኮበለለ። ከብዙ ዓመታትም በኋላ ወደ አባቱ ቤት ሲመለስ ጭር ባለው በረሃ ብቻውን ተኝቶ ሳለ ከእግዚአብሔር መልአክ ጋር ታገለ። መልአኩም አላሸነፈውም። «ስምህ ማነው?» ብሎ ሲጠይቀው፤ «እኔ ያእቆብ ነኝ» አለው። «ከዛሬ ጀምሮ ያእቆብ አትባልም እስራኤል ተብለህ ነው የምትጠራው፤ሰውንም አምላክንም አሸንፈሃልና» ብሎ እግዚአብሔር ኃይሉን አስታጥቆ ሰደደው። ሙሴ የፈረኦንን ቁጣ ፈርቶ ወደ በረሃ ከኮበለለ በኋላ ለብዙ አመታት በግ እየጠበቀ ከቆየ በኋላ በፈረኦን ስር ያሉትን የእስራኤል ልጆች ነጻ እንዲያወጣ እግዚአብሔር ሙሴን በኮሬብ ተራራ ላይ ኃይሉን አስታጠቀው። ለሚታመኑበት ሁሉ እግዚአብሔር ኃይሉን ሊያስታጥቃቸው ታማኝ ነው።

እኔ ተወልጄ ያደግሁት ወሎ ክፍለ ሃገር ሰቆጣ አውራጃ ኮላን በምትባል ቀበሌ ነበር። በ1921 ዓ.ም. «በአስመራ ከተማ የአድቬንቲስት ቤ/ክ አለ» በተባለ ጊዜ አለቃ ምትኩ ወልደ ጊዮርጊስ እና አቶ ኃይሉ ወርቅነህ የተባሉ ጥንት አባቶቻችን ለቤተሰብና ለወገኖች ሳይናገሩ የሃይማኖት ትምህርት ለመማር ሄደው ክረምቱን ከርመው ተመለሱ። የአድቬንቲስትንም የሃይማኖት ትምህርት ተቀብለው እንደመጡ በአካባቢያችን ይህንን በድብቅ ማስተማር ጀመሩ። በ1928 ዓ.ም. ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ «እንግዳ የሃይማኖት ትምህርት በማስተማር የሚረብሹ ሰዎች አሉ» በማለት በጣልያን ጊዜያዊ መንግሥት ተከሰው እስር ቤት ገቡ። ውሳኔ ሳይሰጣቸው የኢትዮጵያ መንግሥት አገሩን ሲያስመልስ በዚያ ምክንያት ተፈቱ። በድጋሚ በ1945 ዓ.ም. ሰቆጣ አውራጃ ተከስሰው «ፀረ-ማርያሞች» በመባል ከእስር ቤት አስቀመጡአቸው።

ለብዙ ጊዜ ከታሰሩ በኋላ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው በሚቀጥለው ቀን «ይረሸኑ!» የሚል ትእዛዝ ከወረዳው አስተዳደር ተላለፈ። «በጥንቃቄ እንዲጠበቁ በሰንሰለት ይታሰሩ» የሚልም ትእዛዝ ወጣ። መጀመሪያ የሃይማኖት አባታችንን ኃይሉ ወርቅነህን እግሮቹን በሰንሰለት ሲያስሩት ሰንሰለቱ ከእግሩ ላይ ተሰበረ፤ሌላ አዲስ ሰንሰለት አምጥተው ቢያስሩት በድጋሚ ተሰበረ፤ሶስተኛ ጊዜ አምጥተው ሲያስሩት አሁንም ተሰበረ፤በአራተኛው «እነኚህስ አስማት አለባቸው» ተብሎ ወደ ወሎ ክፍለ ሃገር ተላኩ። ጥፋት ስላልተገኘባቸው በነጻ ተለቀቁ። እንደገና ተመልሰው ወንጌልን ማስተማራቸውን ቀጠሉ። እኔ ተወልጄ በአደግሁባት መንደር 42 ሰዎች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ አስረከቡ እኔም በዚያን ወቅት ነበር ጌታ የሱስ የግል መድሃኒቴ እንዲሆን የወሰንኩት።

ከ1945-52 ዓ.ም. ድረስ ከባድ የሃይማኖት እንቅስቃሴ ተደርጎ ነበር። በዚያም ምክንያት ፀረ-ክርስቲያን እንቅስቃሴ ይካሄድ ነበር። የአድቬንቲስት ቤ/ክ ምስረታም ሲጀመር በመንግሥት ትእዛዝ መሠረት ከእህል እስከ እንስሳ ድረስ እንዲዘረፉ ትእዛዝ ወጣ። በእኔና በሌሎች አድቬንቲስት ወንድምና እህቶቼ ላይ ስደት ተነሳ። እንደተባለውም አንድ ነገር እንኳን ሳይተዉልን ንብረታችንን ሁሉ ወሰዱብን፣ጎተራችንንም አፈረሱብን፣ከብቶቻችንም አንድ ሳይቀር ታረዱ። ከዚያም ወደ ጎረቤት መንደር ተሰደን በዚያ ተደብቀን እያለን አንድ አስገራሚ ነገር ተሰማ። «ሃብት ንብረታችሁን እንመልስላችኋለን፣መጥታችሁ እኛ ለምናዛችሁ ለሊባኖስ ስገዱ የኛን አምልኮ ተከተሉ ያለዚያ ባስቸኳይ ይህን መንደር ልቀቁ! ባትለቁ ግን እንደከብቶቻችሁ ትታረዳላችሁ!» የሚል መልእክት መጣልን። አራት አዛውንት እናቶቻችን (ወ/ሮ ላቀች እርታ፤ወ/ሮ አስረበብ አካሉ፣ወ/ሮ ባዩሽ ዘገየ እና ወ/ሮ እማሆይ አለማየሁ) «ቤታችን ዋሻና ጫካ ይሆናል እንጂ ለእናንተ አምላክ አንሰግድም!» በማለት ወደ ተከዜ ወንዝ በሚገኘው በረሃ በዋሸዬ ለ12 ቀናት እራሳችንን በመሰወር ያችን የጭንቅ ጊዜ አሳለፍን።

የሚገርመው ነገር በዋሻ ውስጥ ሳለን ከሕጻናት ጀምሮ እስከ አዋቂ ድረስ «እንጀራ አምጡ» የሚል አንድ እንኳ አልነበረም። ሙጫና የዱር ፍሬ በመብላት እንደሰት ነበር። ትልቁ ፍርሃት የነበረው «ሽፍቶች መጥተው ቢጠይቁን ምን እንሆናለን?» የሚለው ነው። በዚያን አስጨናቂ ጊዜ ግን አምላክን ሌትና ቀን ከመለመን በስተቀር ሌላ ቁም ነገር አልነበረንም።

በዘመናችንም ዘንዶው (ሰይጣን) የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትንና የየሱስ ምስክርነት ባላቸው ክርስትያኖች ላይ ተቆጥቷል (ራእይ 12፣17)። ይህንን ታላቅ ዘንዶ የሚቋቋመው በቀራንዮ መስቀል ላይ የተሰቀለው ጌታ የሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ዛሬ ከመቸውም የበለጠ እራሳችንን ሕያው መስዋእት አድርገን ለእግዚአብሔር ልናስረክብ ይገባናል። ምክንያቱም የመዳን ቀን ዛሬ ነው። የጠፉትን የምንፈልግበት ፣ የተበታተንነውም በመንፈስ አንድ የምሆንበት ፣ ለታላቁም የመከራ ጊዜ የምንዘጋጅበት ጊዜ አሁን ነው።

ምንም እንኳን አሁን ባለሁበት ከተማ ብዙ ፈተናዎች ቢኖሩም በየአመቱ ጌታ አንዳንድ ደረጃዎችን እያዘለለኝ ወደ ሙላቱ ወደ የሱስ ክርስቶስ በመገስገስ ላይ እገኛለሁ። እንቁላል በፈላ ውሃ ሲቀቀል ይጠነክራል እንጂ አይላላም። የሚያጠነክረውም ያ የፈላ ውሃ ነው። እንዲሁም የክርስቶስ አገልጋዮች ሁሉ በፈተና ባለፉ ቁጥር ይጠነክራሉ። እግዚአብሔርም ኃይልን ይሰጣቸዋል። ለሚታመኑበት ሁሉ አምላክ ኃይሉን ያስታጥቃቸዋል።

እንግዲህ ወንድሞቼና እህቶቼ ምኞታችንና ትግላችን በሰው ልብ ያልታሰበችውን ፣ ጆሮም ሰምቶ የማያውቃትን ፣ አይንም ያላያትን እግዚአብሔር ለሚወዱት ወደ አዘጋጃት አገር ለመድረስ ነው። ለዚያ የምንዘጋጅበት ጊዜ ዛሬ ነው። ይህንን ለሚያነቡ ሁሉ ላሳስብ የምፈልገው ነገር አለኝ፥ አሁን ባለሁበት አገር ዘንዶው መረቡን ዘርግቶ እየተፈታተነን ያለበት አገር ውስጥ ነው። ስለዚህ ለጌታ ሥራ ብርታትን እና ድፍረትን እንዳገኝ በጸሎታችሁ አስቡኝ። ◆

*ጌቱ ካሳ (ከእስራኤል)*

***ውድ አንባቢ፥***
***የእርስዎንም ታሪክ ጌታ የሱስ እንዴት እንደቀየረውና የሰማይ ቤት ወራሽ እንዲሆኑ እንዳደረግዎ ለአንባቢያን ለማሳወቅ ፈቃድዎ ከሆነ ምስክርነትዎን በጽሁፍ ላኩልን***

## የሃይማኖቱ ዓለም ወቅታዊ ዜናዎች

### ☛ 15000 ሰዎች ሕይወታቸውን ለየሱስ አስረከቡ

ባለፈው ዓመት በመስከረም ወር በ ኦንጎሌ (በሕንድ አገር የሚገኝ ከተማ) በተደረገው የወንጌል ጥረት ላይ ከ15000 ሰዎች በላይ ተጠምቀው የሰባተኛው ቀን አክባሪ አድቬንቲስት ቤ/ክ አባል ሆነዋል። ሌሎች ወደ 5000 የሚሆኑ ሰዎች ደግሞ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ እንደሚጠመቁ ፈቃደኛነታቸውን ገልጸዋል። በሕንድ አገር ያለችው አድቬንቲስት ቤ/ክ አባላት ቁጥር በፍጥነት በመጨመሩ 100 አዲስ ቤተክርስቲያኖች መገንባት ይኖርባቸዋል። *(ANN)*

### ☛ ቅዱሱ የኢንተርኔት ጠባቂ

ጳጳስ ጆን ፓውል II የሴቪላውን ቅዱስ ኢሶዶርን «የኢንተርኔት ጠባቂ» እንዲሆን መረጡ (ሰየሙ)። በ7ኛው ክፍለ ዘመን ይኖር የነበረው ኢሶዶር የመጀመሪያውን ኢንሳይክሎፔዲ የሠራ ሰው ሲሆን፤ወደፊት በኮምፒውተር የሚጠቀሙ ሰዎችን ከኮምፒውተር ቫይረስ፣ብልሽት እና ስህተቶች ይጠብቃቸዋል (ይከላከልላቸዋል) ተብሎ በካቶሊክ ቤ/ክ ይታመናል። *(tomorrow)*



### ☛ መጽሐፍ ቅዱስ በ2262 ቋንቋዎች

በአሁኑ ጊዜ ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ወይም አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በ2262 ቋንቋዎች ተተርጉመዋል። «ባለፈው ዓመት ብቻ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ 28 ቋንቋዎች ተተርጉሞታትሟል» ሲል በሽቱትጋርት የሚገኘው የጀርመን የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር አስታወቀ። በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ላይ የሚገኙት ቋንቋዎች ቁጥር 6500 ይገመታል። *(dpa)*



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# የትንቢት ቃል


Yetnbit Kal
P.O.Box 1749
90006 Nuernberg
Germany

Editors:
Dawit Mehari
Dawit Mengistu

Tel & Fax 0049 - 911- 41 57 89
Tel & Fax 0049 - 89 - 22 24 48
E-Mail: dawit.mehari@mail.com
E-Mail: dawid.m@relax-online.de


ይህች «የትንቢት ቃል» የምትለው የአድቬንቲስት መጽሔት በጀርመን አገር ተዘጋጅታ በየሶስት ወር ትወጣለች። አላማዋም በአገራችንና በተለያዩ አህጉራት የሚገኙትን ወገኖቻችንን ለየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለማዘጋጀት ነው። ምንም ዋጋ የማይከፈልባት በነጻ የምትላክ እንደሆነች ልንገልጽልዎ እንወዳለን። ስለዚህ ለእርስዎም ሆነ ለሌሎች ጽሑፉ እንዲደርሳቸው ለሚፈልጉት ሰዎች አድራሻዎችን ቢያሳውቁን መጽሔቱን እንልካለን።

በዚህች መጽሔት መልእክት ተባርከው እንደሆነና አስተያየትም ሆነ ጥያቄ ካለዎ ሃሳብዎን ቢገልጹልን በጣም ደስ ይለናል።

## «የተስፋ ድምጽ» ዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ
### አዲስ የስርጭት ሰዓትና መስመር

በእርግጥ በዚህች ግዙፍ አለም ወንጌል የሚሰበክበት ወቅት ይመጣ ይሆን? አዎ! እነሆ አለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ በአለም አቀፍ ደረጃ በ45 ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ወንጌልን ይዘራል። እርስዎስ የየትኛው ቋንቋ ተናጋሪ ነዎት? በሚከተሉት መስመሮች በሰዓታችን በአየር ላይ ይፈልጉን። በእርግጥም ከልዩ የፍቅር መልእክቶቻችን ጋር ያገኙናል። የስርጭቱ መስመርና ሰዓትም በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር እንደሚከተለው ነው፥

| ቋንቋ | ሠዓት | ሜትርባንድ | ፍሪኩዌንሲ KHz |
|---|---|---|---|
| አማርኛ | ጠዋት 12:00-12:30 | 25 | 11710 |
| አማርኛ | ጠዋት 12:30-1:00 | 41 | 6155 |
| አማርኛ | ምሽት 1፤00-1፤30 | 19 | 15115 |
| አማርኛ | ምሽት 2:00-2:30 | 19 | 15460 |
| ኦሮምኛ | ምሽት 12:30-1:00 | 25 | 12020 |
| ትግርኛ | ምሽት 12:30-1:00 | 19 | 15115 |
| ትግርኛ | ምሽት 2:30-3:00 | 19 | 15460 |
| አፋርኛ | ምሽት 12:00-12:30 | 19<br>16 | 15115<br>17560 |

ይህንን የጽሑፍ አገልግሎት በገንዘብ ለመደገፍ የምታስቡ ሁሉ በዚህ የባንክ ቁጥር መጠቀም ትችላላችሁ። ለድጋፋችሁ በቅድሚያ ከልብ እናመሰግናለን እግዚአብሔር ይባርካችሁ!
Sparkasse Nürnberg,
Yetnbit Kal,
Account Nr.: 3 516 113
BLZ: 760 501 01

## የጥያቄዎ መልስ

## «ክርስትያኖች ሁሉ በስውር ይነጠቃሉን?»
*አቶ ጀ. ከ. ከጀርመን*

ስውር መነጠቅ» የሚለው ቃል በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አይጠቀስም። ይህ በዘመናችን የሚኖሩ አንዳንድ ክርስትያኖች የሚናገሩት አሳብ (አስተያየት) ነው። በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ የተሃድሶ መሪዎችም ይህንን ቃል አያውቁትም። «ስውር መነጠቅ» የሚለው አባባል በፕሮቴስታንት ቤ/ክ ውስጥ የተስፋፋ «ከክርስቶስ ተቃዋሚ» (Antichrist) እና «ትንቢትና እስራኤል» ከሚለው ጋር የሚገናኝ ትምህርት ነው። ስለዚህ ነጥብ ጠንቅቆ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ወደፊት የሚሆኑት ነገሮች እኛ ካመንነው ውጪ ሆነው ከተከሰቱ ልናዝንና ተስፋ ልንቆርጥ እንዲሁም ደህንነትን ሳናገኝ ልናልፍ እንችላለን። በእምነታችንም ላይ ተጽእኖ ሊያመጡብን ይችላሉ። በመሆኑም «መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መነጠቅ ምን ይላል?» ብለን ልንጠይቅ ይገባናል።

ጳውሎስ በ 1ኛ ቆሮ 15፤51-52 ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ በሕይወት ያሉት ክርስትያኖች «እንደሚለወጡ» ይናገራል። የሚለወጡትም ከመነጠቃቸው በፊት ነው። የኋለኛው መለከት ሲነፋ የሞቱት ክርስትያኖች «በድንገት በቅጽበት አይን» ይነሳሉ (ቁ.22+23)። ክርስቶስ ሲመጣ በሕይወት የሚኖሩት ክርስትያኖች ደግሞ ይለወጡና ልክ ከሞት እንደተነሱት ጻድቃን የማይሞተውንና የማይበሰብሰውን አካል ከእግዚአብሔር ይረከባሉ። የዚያን ጊዜ ሞት በማያዳግም ሁኔታ (ለዘላለም) ድል በመነሳት ይዋጣል (ቁ.53-54)።

ጳውሎስ ይህንን የሚያስደንቅ ትርኢት በ 1ኛ ተሰ 4፤13-18 በዝርዝሩ ገልጾታል። ጌታ እስኪመጣ ድረስ በሕይወት የሚኖሩት ክርስትያኖች የሞቱትን (ያንቀላፉትን) አይቀድሙም። ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት እና ሙታን ከመነሳታቸው በፊት ያልሞቱት አስቀድመው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገቡም። የእግዚአብሔር መለከት ሲነፋ ጌታ ራሱ ከሰማይ ወደ ምድር ይመጣል። በዚያን ጊዜ በጌታ ያንቀላፉት በመጀመሪያ ይነሳሉ። ከዚያም በሕይወት ካሉት ክርስትያኖች ጋር አብረው ጌታን በአየር ለመቀበል ይነጠቃሉ።

የየሱስ ዳግም ምጽአት፤የሙታን ትንሳኤ፤በሕይወት የሚኖሩት ክርስትያኖች መለወጥ እና መነጠቅ ተነጣጥለው መታየት የለባቸውም። እነዚህ በተለያዩ ጊዜያቶች የሚከሰቱ ሳይሆን በአንድ ጊዜ የሚከሰቱ ነገሮች ናቸው። እንዲሁም በስውር የሚሆኑ ወይም ማንም ሰው ሳያስተውል የሚፈጸሙ ነገሮች አይደሉም። የዓለማችንን ፍጻሜ የሚያሳዩና የእግዚአብሔር መንግሥት መጀመሩን የሚገልጹ ሁኔታዎች በስውር የሚከሰቱ ነገሮች አይደሉም። ዳንኤል በምእራፍ 2 ላይ የየሱስን ተመልሶ መምጣት «ከተራራው የተፈነቀለውንና የምድርን መንግሥታት ሁሉ ከሚያጠፋውና ለዘላለም የማይፈርሰው መንግሥት ምሳሌ ከሆነው ድንጋይ ጋር ይመስለዋል» በራእይ 19 ላይ ደግሞ የሱስ በሰማይ ካሉት ጭፍራዎቹ ጋር ተመልሶ እንደሚመጣ ተጽፎ እናገኛለን (ቁ. 11-16)። ይህ ለብዙ ሰዎች የሚያስደነግጥ ሁኔታ ነው። የሱስም « ... የሰው ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ የምድር ወገኖች ሁሉ ያዩታል፤መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምጽ ጋር ይልካቸዋል ከሰማያትም ዳርቻ እስከዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ» ይላል። ሃጥአንም በዚያን ጊዜ በድንጋጤ መንፈስ እንደዚህ ብለው ይጮሃሉ፥ «ተራራዎችና አለቶችንም በላያችን ውደቁ! በዙፋኑም ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቁጣ ሰውሩን! ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና ማንስ ሊቆም ይችላል?» (ራእይ 6፤16-17) ይህ አስገራሚ ትእይንንት በስውር የማይሆን ነገር ነው።

«ጌታን በአየር ለመቀበል እንነጠቃለን» (1ኛ ተሰ 4፤17) የሚለው አባባልም ምስጢራዊና በስውር የሚሆን አይደለም። ይህን የበለጠ ለመረዳት ማቴ 24፤29-31, ሉቃ 21፤26-27, እና ራእይ 1፤7 ን ያንብቡ። እነዚህ ሁሉ ጥቅሶች እንደሚያሳዩት ጻድቃን በድል ከክርስቶስ ጋር ወደ ሰማይ ይሄዳሉ። አንዘንጋ! የሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ዘላለማዊ መንግሥቱ የሚወስዳት ማንም ሳያስተውለው በስውር ሳይሆን ሙሽራ ሙሽሪትን እንደሚወስዳት በክብር ነው።

እንዲሁም «በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ እንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች» የሚለውም ጥቅስ (ማቴ 24፤40-41) በስውር ስለመነጠቅ ለመግለጽ የተጻፈ ሳይሆን የየሱስ ዳግም ምጽአት ድንገተኛና ባልታሰበ ሰአት እንደሚሆን ለማስረዳት የታሰበ ጥቅስ ነው። ይህንን ለመረዳት የምእራፉን ይዘት እና የሱስ የተናገራቸውን ጥቅሶች ሁሉ በአንድ ላይ ማንበብ ያስፈልጋል። ◆

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com